11 ኛ ዓመት ቁጥር 14

11th Year No. 14

ባህር ዳር መጋቢት 30 ቀን 1998 ዓ.ም

Bahir Dar 8 April, 2006

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State

## in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት

የፖ.ሣ.ቁ 1324

ያንዱ ዋጋ ብር 8.20

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር **129/1998** ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ፅ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ

አዋጅ ቁጥር 129 /1998 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

ከአማራ ብሔራዊ ክልል ከተሞች ቁልፍ ችግሮች አንዱ ከፍተኛ የቤት እጥረት መኖሩና የችግሩም ዋነኛ ተጠቂ በዝቅተኛና መካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኘው ነዋሪ ህብረተሰብ በመሆኑ፤

የቤት እጥረቱን ማቃለል ይቻል ዘንድ ችግሩ ለተባባሰባቸው ከተሞች ቅድሚያውን ሰጥቶ ወጭ ቆጣቢ የሆኑ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም በዋነኛነት ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸው የከተማ ነዋሪዎች አገልግሎት የሚውሉና ደረጃቸውን የጠበቁ ቤቶች እንዲገነቡ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑና በየከተሞቹ ለሚከናወነው የቤት ግንባታ የክልሉ መንግስት ቀጥተኛ ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባ በመታመኑ በከተሞች የሚካሄደው የቤት ግንባታ የከተማውን መሪ እቅድም ሆነ የነዋሪውን ህዝብ አቅምና ፍላጎት መሠረት በማድረግና የኮንስትራክሽን ዘርፉን በሚያስፋፋና በሚያጠናክር፣እንደዚሁም ሰፊ የስራ እድል መፍጠር በሚያስችል መልኩ መከናወኑ አስፈላጊ ስለሆነና ይሄው ተፈጻሚ እንዲሆን የክልሉ መንግስት ሰፊ ሚና መጫወት ያለበት ሆኖ በመገኘቱ፤

በመንግስት የሚካሄደው የቤቶች ግንባታ በክልሉ ከተሞች ውስጥ ያለውን የቤት እጥረት በአጭር ጊዜ ለማቃለል እንዲያስችልና ግንባታውም በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲፈጸም እንደዚሁም በከተሞች ተመጣጣኝ የቤት ልማት እንዲኖርና የተቀናጀ ፕሮግራምና እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ የማድረግ

ኃላፊነት የተሰጠውና ራሱን የቻለ የፕሮጀክት ፅ/ቤት በህግ ማቋቋም በማስፈለጉ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3(1) ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

**1.** አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ‘የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ፅ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 129/1998 ዓ.ም’ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2.** ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፥-

1. ‘የከተማ አስተዳደር’ ማለት በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ከተሞች ማቋቋሚያ፣ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት

   መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 91/1996 ዓ.ም /እንደተሸሻለ/ መሰረት በህግ በታወቀ ወሰን ተደራጅቶ የአንድን ከተማ ነዋሪ ህዝብ የፖለቲካ፣የአስተዳደር፣የልማትና የአግልግሎት አሰጣጥ ስልጣንና ኃላፊነት በመረከብ የሚመራ የአካባቢ አስተዳደር ነው፡፡
2. ‘ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያከው የከተማ ነዋሪ’ ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (1) ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት የክልሉ መስተዳድር ምክር

| | |
|---|---|
| ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰነው ነው፡፡<br>3. ‘ቢሮ’ ማለት የክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ነው፡፡ (በአዋጅ ቁጥር 177/2003 ተሸሯል)<br><br>ክፍል ሁለት<br>ስለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ መቋቋም፣<br>ተጠሪነት፣አላማ፣አወቃቀርና ሥልጣን<br>**3.** መቋቋምና ተጠሪነት<br>1. የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት /ከዚህ በኋላ ‘ጽህፈት ቤቱ’ እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡<br><br>2. የጽ/ቤቱ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል፡፡(በአዋጅ ቁጥር 177/2003 ተሸሯል)<br>3. ጽ/ቤቱ የተቋቋመው ለአምስት ዓመታት እድሜ ነው፡፡<br>**4.** የጽ/ቤቱ አላማ<br>ጽ/ቤቱ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡-<br>1. እየተባባሰ የመጣውን የመጠለያ ችግር ለማቃለል በሚያስችል ሁኔታ ወጭ ቆጣቢ የሆኑ ቴክኖሎጅዎችንና የሰውን ጉልበት በስፋት በመጠቀም ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸው የከተማ ነዋሪዎች አገልግሎት የሚውሉ ቤቶች በመገንባት በአጭርና በረጅም ጊዜ የቤት ባለቤት ማድረግና፤<br>2. የቤት ልማቱ ፕሮግራም ሰፊ የሥራ እድል በሚፈጥር መንገድ እንዲከናወንና ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን | |

በፕሮግራሙ በማሳተፍ እነዚሁ ተቋማት እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር።

**5.** የጽ/ቤቱ አድራሻ

የጽ/ቤቱ አድራሻ በባህር ዳር ከተማ ውስጥ ይሆናል።

**6.** የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ጽ/ቤቱ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት

ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በየከተሞቹ ያለውን የቤት እጥረትና እጥረቱን ለማቃለል መንግስት ሊመድበው የሚገባውን በጀትና ሊያደርገው የሚገባውን ድጋፍ፣እንደዚሁም ለጽ/ቤቱ ስራ የሚያስፈልገውን በጀት አጥንቶ በቢሮው በኩል ለክልሉ መንግስት ያቀርባል።ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣አጠቃቀሙን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል።
2. ከየከተሞቹ መሪ ፕላኖች ጋር የተጣጣሙና ለከተማ ውበት አዎንታዊ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የቤት ዲዛይኖችን ወጭ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤
3. ወጭ ቆጣቢ የሆኑ ቴክኖሎጅዎችንና የግንባታ ግብአቶችን በመጠቀም በየከተሞቹ ደረጃቸውን የጠበቁ ቤቶች እንዲገነቡ ያደርጋል።
4. የቤቶችን ልማት ለማከናወም የሚያስፈልገው የፋይናንስ አቅርቦት የሚገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
5. ከዲዛይን እስከ ኮንስትራክሽን ያሉት የስራ ሂደቶች ደረጃ በደረጃ እንዲፈጸሙና የግንባታ ፕሮግራሙ በቅልጥፍና

እንዲከናወን ተገቢውን ስልት ይቀይሳል፣በስራ ላይ ማዋሉን ያረጋግጣል፡፡

6. በገበያ ላይ እጥረት ያለባቸውን የግንባታ ግብአቶች ጥቅል ግዥ በመፈጸም የዋጋና የዕቃ ጥራት ተጠቃሚ መሆን የሚቻልባቸው ሁኔታዎች ሲኖሩ ከሃገር ውስጥና ከውጭ አገር እቃዎችን ገዝቶ ለሚመለከተው የከተማ ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች ያስረክባል፡፡
7. በየከተማ አስተዳደሮቹ ዘንድ በክልሉ መንግስት ድጋፍ የሚከናወኑ የቤት ልማት ፕሮግራሞች ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን በሰፊው የሚያሳትፉ እንዲሆኑ አመች የአሰራር ሥርአቶችን ይዘረጋል፣ተፈጻሚነታቸውን ይከታተላል፡፡
8. በቤት ልማቱ ዘርፍ የተሰማሩና የሚሰማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያስተባብራል፣አስፈላጊ ድጋፎችን እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
9. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለተቀናጀ የቤት ልማት እንቅስቃሴ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያላቸውና ለተለያዩ አግልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ህንጻዎች እንዲገነቡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

10. ይህንን አዋጅ መሰረት በማድረግ በከተማ አስተዳደሮች ስር በተቋቋሙ የቤት ልማት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ጽ/ቤቶች አማካኝነት የሚገነቡ ቤቶች ተገቢውን የጥራት ደረጃ ጠብቀው መሠራታቸውን

ያረጋግጣል፣የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል።

11. ግንባታቸው የተጠናቀቀላቸው ቤቶች ከተሟሉ መረጃዎች ጋር በሚመለከታቸው ከተማ አስተዳደሮች በኩል በወቅቱና በህጋዊ መንገድ ለተጠቃሚዎች የሚተላለፋበትን ምቹ ሁኔ ይፈጥራል።

12. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣በህግ መሰረት ውል ይዋዋላል፣በስሙ ይከሳል፣ይከሰሳል፤

13. አላማዎቹን ለማሳካት የሚያስፈልጉ ሌሎች ህጋዊያን ተግባራትን ያከናውናል።

**7.** ድርጅታዊ አቋም

ጽ/ቤቱ በርዕሰ መስተዳደሩ የሚሾም የራሱ ስራ አስኪያጅ፤አስፈላጊ የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሰራተኞች ይኖሩታል።

**8.** የጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር

1. የጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ዋና ስራ አስፈጻሚ በመሆን የጽ/ቤቱን ሥራዎች

በበላይነት ይመራል፣ሰራተኞቹን ያስተዳድራል፣ይቆጣጠራል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ አስኪያጁ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ሥር ለጽ/ቤቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ለማስፈጸም በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

   ሀ/ የጽ/ቤቱን ድርጅታዊ መዋቅር፣ደመወዝ፣አበልና ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች አያዘጋጀ በቢሮው በኩል ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በማቅረብ ያስወስናል፤

   ለ/ በጽ/ቤቱ ስም የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ይህንኑ

| | |
|---|---|
| የሚያንቀሳቅሱ ሰዎችን ይሰይማል፣ሂሳቡ በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል፣<br>ሐ/ የጽ/ቤቱን የረጅምና የአጭር ጊዜ የስራ ፕሮግራም የማስፈጸሚያ በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤<br>መ/ ለጽ/ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፣<br><br>ሠ/ ለሥራ አስኪያጁ ተጠሪ የሆኑትን የሥራ ኃላፊዎች ቅጥርና ስንብት ለቢሮው አቅርቦ ያስጸድቃል፤<br>ረ/ ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥር 'ሠ' ሥር የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የጽ/ቤቱን ሌሎች ሰራተኞች ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፣ያሰናብታል፤<br>ሰ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ጽ/ቤቱን ይወክላል፤<br>ሸ/ የጽ/ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቢሮው፣ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ያቀርባል፤<br>ቀ/ በቢሮው የሚሰጡጥን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡<br>3. ሥራ አስኪያጁ ለጽ/ቤቱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ስልጣንና ተግባራቱን በከፊል ወይም በሙሉ ለበታች የስራ ኃላፊዎች በውክልና መስጠት ይችላል፡፡<br><br>ክፍል ሦስት<br>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች<br>**9.** ስለ በጀት<br>የጽ/ቤቱ የበጀት ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ፡- | |

1. በክልሉ መንግስት የሚመደብ ሃብት፤
2. የቤት ልማቱን ለማገዝ ከለጋሽ ድርጅቶች የሚገኝ ድጋፍ ፤
3. ሌሎች

**10.** ስለሰው ሃይል ቅጥርና አስተዳደር

የጽ/ቤቱ ሰራተኞች ቅጥርና አስተዳደር በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ህግ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

**11.** የሂሳብ መዛግብት

1. ጽ/ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፡፡
2. በሂሳብ መዛግብቱና በገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች አያያዝና አጠባበቅ ረገድ ጽ/ቤቱ ተቀባይነት ያላቸውን የድርብ ሂሳብ አሰራር መርሆዎች ይከተላል፡፡

**12.** የሂሳብ ምርመራ

የጽ/ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየጊዜው ይመረመራሉ፡፡

**13.** የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ጽ/ቤቱ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜና ሁኔታ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**14.** ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ህግ፣ደንብ፣መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ

የተሸፈኑትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**15.** ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1. ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን ደንቦች የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ቢሮው ለአዋጁና በአዋጁ መሰረት ለሚወጡ ደንቦች ተፈጻሚነት የሚረዱ ዝርዝር መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን አለው፡፡

**16.** አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

መጋቢት 30 ቀን 1998 ዓ.ም

አያሌው ጎበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልል

ፕሬዚዳንት